እነሆ የእሳት ጌታ ካልሆነ በቀር ማንም በእሳት መቅጣት አይገባውም።" አሉ።

ከኢብኑ መስዑድ - አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ ብለዋል፡- «ጉዞ ላይ ከአላህ መልክተኛ -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና - ጋር ነበርን። እርሳቸው ለመፀዳዳት ሄዱ። እኛም ትንሽዬን ወፍ ከነሁለት ጫጩቶቿ
ተመለከትንና ጫጩቶቿን ወሰድን። ወፏም ክንፏን እያራገበች በራ መጣች። ነቢዩም -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና - እንዲህ አሉ: "ይህቺን ወፍ ልጆቿን ወስዶ ያስደነገጣት ማነው? ልጆቿን መልሱላት።" ጉንዳኖች ወረውት በእሳት ያቃጠልነውን ስፍራም ተመልክተው እንዲህ አሉ: "ይህንንስ ያቃጠለው ማነው?" እኛም "እኛ ነን።" አልን። እርሳቸውም: " እነሆ የእሳት ጌታ ካልሆነ በቀር
ማንም በእሳት መቅጣት አይገባውም።" አሉ።» [ሶሒሕ ነው።] [አቡዳውድ ዘግበውታል።]

ዐብደላህ ቢን መስዑድ - አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና - እንዳወሱት ጉዞ ላይ ከነቢዩ -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና - ጋር ሳሉ ነቢዩ -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና - ለመፀዳዳት ሄዱ። ሶሓቦችም ትንሽዬ ወፍ ከነሁለት ጫጩቶቿ አገኙና ጫጩቶቹን ይዘው ሄዱ። ወፏም ጫጩቶቿን በማጣት ድንጋጤ ክንፏን እያራገበችና ዘርግታ እየበረረች መጣች። ነቢዩም -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና - መጡና እንዲህ አሉ: ማነው ልጆቿን በመውሰድ ያሳዘናትና ያስፈራራት? ቀጥሎ እንዲመለሱላት አዘዙ። ቀጥለው በእሳት የተቃጠለ ጉንዳኖች የወረሩት ስፍራ ተመለከቱ። ነቢዩም -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና - "ማነው ይህንን ያቃጠለው?" አሉ። አንዳንድ ሶሓቦችም "እኛ ነን።" አሉ። እርሳቸውም "እሳትን ከፈጠረው ከአላህ በቀር አንድም ሰው በህይወት ያለን በእሳት ሊቀጣ አይፈቀድለትም።" አሉ።

http://www.sunnah.global/hadeeth/am/show/8892